# ዜና አመዝኤ



የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ፣ ቅፅ 13 ቁጥር 6 የካቲት 1999

## በመንግሥትና የሰብዓዊ ዕርዳታ ተባባሪዎች አዲስ የተቀየሰውን የአደጋ ምላሽ አሠራርን በቅንጅት ለመተግበር ተስማሙ

### ከክልል የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ምግብ ዋስትና ቢሮ ሀላፊዎች ጋርም ውይይት ተደርጓል

መንግሥትና የሰብዓዊ ዕርዳታ ተባባሪዎቹ ፣ የድርቅና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎችን እንደየአመጣጣቸው ለመከላከልና ተገቢውን ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችል አዲስ የተቀየሰውን አደጋዎችን የቀጥታ አግባብ ባላቸው ወገኖች እና እንደየአደጋው ባህሪ ምላሽ የመስጠት አሠራርን (Cluster Approach) ተጠያቂነት ፣ ግልፅነትና የተጠናከረ ቅንጅት በተመላበት ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ተስማምተዋል።



ከየካቲት 29-30/1999 ዓ.ም በሒልተን ሆቴል በተካሄደው ዐውደ ጥናት ላይ እንደተመለከተው አዲሱ የአደጋ ምላሽ አሠራር ስልት የተሻለ የአደጋ ጊዜ ምላሽ ዝግጁነት፣ የላቀ ተጠያቂነት ፣ ጠንካራ አብሮ የመሥራት መንፈስ ፣ ብቃት ያለው አመራር እና አስተማማኝ የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ ምላሽ አቅም ለማኖር የሚያስችል በሰብዓዊ ዕርዳታ ሥራ ላይ የተሰማሩ የተመድ ልዩ ልዩ አካላት ዓለም አቀፍ እና ሀገር በቀል የዕርዳታ ድርጅቶች በመንግሥት አስፈፃሚ አካል አስተባባሪነትና አመራር ሰጭነት ምግብና ምግብ ነክ ባልሆኑ የዕርዳታ ፍላጎቶች ረገድ በየተሰማሩበት ዘርፍ በቅንጅትና በጋራ የሚተገብሩት አዲስ የአሠራር ዘዴ ነው።

በዚሁ የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች የተመድ ልዩ ልዩ አካላት ተጠሪዎችና በሰብዓዊ ዕርዳታ ሥራ ላይ የተሰማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊዎችና ተወካዮች በተሳተፉበትና ለሁለት ቀናት በቆየው ዐውደ ጥናት መዝጊያ ላይ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ እንደተናገሩት የክለስተር አሠራር በዘርፉ የተሰማሩትን አካላት ተጠያቂነት ያለበትን አሠራር የሚያጠናክር ብቻ ሳይሆን በመንግሥትና በሰብዓዊ ዕርዳታ ላይ በተሠማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ዘንድ የተሻለ ግልጽነት የሰፈነበት አሠራር እና ብቃት እንዲኖር የሚያደርግ ነው።

በዚህ ዕትም ውስጥ

ባለፉት 6 ወራት 57 ሺህ 941 ሜ/ቶን እህል ለምግብ ዋስትና አቅርቦትና ከ17 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ምግብ ነክ ላልሆነ ፍላጎት በዕርዳታ ተገኝቷል
ገጽ 4

በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ ከብር 69ሚሊዮን በላይ ተለግሷል
ገጽ 5

በአደጋ መከላከልና ዝግጁነት
ኤጀንሲ ህዝብ ግንኙነት
የሚዘጋጅ
ስልክ. 5529259
ጠ.ሳ.ቁ 5686
ድረገጽ፣ www.dppc.gov.et

**መንግሥትና የሰብዓዊ ዕርዳታ ተባባሪዎቹ ፣ የድርቅና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎችን እንደየአመጣጣቸው ለመከላከልና ተገቢውን ወቅታዊ ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችል አዲስ የተቀየሰውን አደጋዎችን የቀጥታ አግባብ ባላቸው ወገኖች እና እንደየአደጋው ባህሪ ምላሽ የመስጠት አሠራርን (Cluster Approach) ተጠያቂነት ፣ ግልፅነትና የተጠናከረ ቅንጅት በተመላበት ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ ተስማምተዋል::**

ዋና ዳይሬክተሩ አያይዘውም አዲሱ የአደጋ ምላሽ አሠራር በየፍላጎት የቀጥታ አግባብ ባላቸው ዘርፎች አስተባባሪዎች (Cluster leads) ግብረኃይሎች እና የሥራ ቡድኖች የሚጠቀሙባቸው ግልጽ የሆኑ የአተገባበር መመሪያዎችን በዝርዝር በማካተቱ በዚህ ረገድ የሚኖረውን ተግባርና ኃላፊነት በብቃት የመወጣት ደረጃን ከፍ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል::



አዲሱ አሠራር በያዝነው ዓመት በመንግሥት ግንባር ቀደም አስተባባሪት ተግባራዊ የሚደረግ ሲሆን ይህም መንግሥት እስካሁን እየሠራበት ያለውን የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት የማስተባበር ሥራ በተሻለ መልኩ ለመተግበር የሚያስችል በመሆኑ ፣ የአደረጃጀትና ከግብረኃይሎች አወቃቀር ጋር የሚጣጣም በመሆኑም አሠራሩን በማጠናከር ውጠ ,ታማ ያደርገዋል ተብሎ ይታሰባል:: አሠራሩ በተለይ በአመዝኤ የሚመራውን የአስቸኳይ ጊዜ አደጋ መከላከል ዕቅድንና ምላሽን ማጠናከርንና መደገፍን ዋንኛ ዓላማው ያደረገ መሆኑም ተመልክቷል::

በዐውደጥናቱ ላይ የተሳተፉት የተባበሩት መንግሥታት ልዩ ልዩ አካላት ሀላፊዎች ፣ በሰብዓዊ ዕርዳታ ሥራ ላይ የተሰማሩ ዋና ዋና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተጠ ሪዎችና የመንግሥት ባለሥልጣናት በአሠራሩ ላይ ሠፊ ውይይት ያደረጉ ከመሆኑም በላይ አዲሱ አሠራር በኢትዮጵያ ውስጥ በተሻለ ደረጃ ተግባራዊ የሚደረግበትን ሁኔታ ለመፈተሽ አደጋን በእንጭጩ ማስቀረት ፣ ውሀና ንጽህና ፣ ጤና ፣ ሥነምግብ ፣ መጠለያ ፣ ሎጅስቲክስ እና የቢሮዎች ደህንነትና ከለላ መስጠት በሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ በሠባት በድኖች ተከፍለው ለተሰጧቸው ምናባዊ የአስቸኳይ ጊዜ አደጋዎች መንግሥት ለሚሰጠው ምላሽ እንዴት የተሻለ ድጋፍ ሊያደርጉ እንደሚችሉ በየቡድኖቻቸው ተወያይተው ባቀረቧቸው የተለያዩ አማራጮች ላይ በተሳታፊዎቹ ሠፊ ውይይት ተደርጓል::

በዐውደጥናቱ ላይ ተሳታፊ የነበሩት የተባበሩት መንግሥታት ሰብዓዊ ዕርዳታዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ ፖል ሀበርት ስለ አዲሱ አሠራር ሲገልጹ “አጠቃላይ የሰብዓዊ ዕርዳታ ሥራ ማስተባበርን እና የአደጋ ምላሽ አቅምን የበለጠ የማጠናከርን አስፈላጊነት በመገንዘባችን መንግሥት በተቻለ መጠን የላቀ የአደጋ ጊዜ ምላሽ አቅም እንዲኖረው የመደገፍ ኃላፊነት አለብን” ብለዋል::

በዐውደጥናቱ ማጠቃለያ ላይም የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ አዲሱ የአደጋ ጊዜ ምላሽ አሠራር የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሚያደርገው ቀጣይነት ያላቸው የአሠራር ማሻሻያዎች አካል እንደ መሆኑ መጠን ሂደቱ ቀጣይ ውይይትንና በየጊዜው መሻሻል የሚገባቸውን አሠራሮች እየፈተሹ ማሻሻልን የሚጠይቅ ነው በማለት ገልፀዋል::

የዐውደ ጥናቱ ተሳታፊዎችም አዲሱ አሠራር በኢትዮጵያ መዘርጋቱ ቁልፍ ሚና የሚጫወት ቢሆንም ወደፊት መሠራት የሚገባቸው በርካታ ነገሮች እንዳሉ መገንዘባቸውን ተናግረዋል፡፡

ይኸ በዚህ እንዳለም በያዝነው የአውሮጠውያን ዓመት መንግሥትና ተባባሪዎቹ በቀየሱት የአደጋ ጊዜ ምላሽ እና የዕርዳታ ፍላጎት አቅርቦት አዲስ አሠራር ተግባራዊ በሚደረግበት ሁኔታ ላይ የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር ከክልል የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ምግብ ዋስትና ቢሮ



ሀላፊዎችና ተወካዮች ጋር ጥር 5 ቀን 1999 ዓ.ም በፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የስብሰባ አዳራሽ ውይይት ተካሂዷል፡፡

በዚሁ ውይይት ላይ የፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ሲሞን መቻለ እንደገለፁት ባለፈው ታህሳስ ወር መጨረሻ ላይ በመላው ሀገሪቱ የተደረገው የመኸር ምርት ግምገማ ውጤት እንዳሳየው የዓመቱ የግብርና ምርት ባለፉት ዓመታት ከነበረው ጋር ሲነፃፀር በእጅጉ የላቀ መሆኑንና ይህም በዓለም እርሻና ምግብ ድርጅት (FAO) ጥናት ጭምር መረጋገጡን ጠቁመው ይህም ባለፉት ዓመታት ከታየው አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ሌሎች ተዛማጅ ውጤቶች ተዳምሮ በሀገሪቱ የሚኖረውን የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ፈላጊ ህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ሁኔታ እንዲቀንስ አስችሏል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ በማያያዝም በተወሰኑ የሀገሪቱ አካባቢዎች ሊኖር ለሚችለው የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት ቀደም ሲል በየዓመቱ በህዳርና በታህሳስ ወሮች በሚካሄድ የአንድ ጊዜ የሀገር አቀፍ ጥናት ውጤት መነሻነት ክልሎች በየወሩ የሚያቀርቡትን ጥያቄ በመመርኮዝ ከፌዴራል አመዝኤ ይላክ ከነበረው የምግብና ምግብ ነክ ያለሆኑ የዕርዳታ ቁሳቁሶች አቅርቦት ለየት ያለ አሠራር የተቀየሰ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ይህም አዲስ በተቀየሰው የዕርዳታ አቅርቦትና አጠቃቀም መሠረትም መንግሥት ፣ ለጋሾችና ተባባሪዎቹ በጥልቀት በጋራ በደረሱት ስምምነት መሠረት እ.ኤ.አ የ2007 የዕርዳታ ፍላጎት መዘጋጀቱንም አብራርተዋል፡፡

በአዲሱ የዕለት ዕርዳታ አቅርቦትና አጠቃቀም የአሠራር ሥርዓት መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ የሚያስፈልግባቸው ሁኔታዎችና አካባቢዎች ከተፈጠሩና የዕርዳታው አስፈላጊነት በክልል መንግሥታት ከተጠየቀ በአጥኚ ባለሙያዎች ችግሩ የደረሰባቸው አካባቢዎች በአካል በመገኘት እያንዳንዱን ቦታ በጥልቀትና በዝርዝር ክለሳ ጥናት ሲረጋገጥ ብቻ አስፈላጊው ምላሽ እንደሚሰጥ ዋና ዳይሬክተሩ አስረድተዋል፡፡

በዚሁ የአሠራር ሥርዓት ውይይት ላይ እንደተመለከተው አሠራሩ እንደቀድሞ በኮታና በመደበኛነት የሚደረግ የዕርዳታ አመዳዳብን የሚያስቀርና ችግር የሚፈጠ



በአዲሱ የዕለት ዕርዳታ አቅርቦትና አጠቃቀም የአሠራር ሥርዓት መሠረት የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ ዕርዳታ የሚያስፈልግባቸው ሁኔታዎችና አካባቢዎች ከተፈጠሩና የዕርዳታው አስፈላጊነት በክልል መንግሥታት ከተጠየቀ በአጥኚ ባለሙያዎች ችግሩ የደረሰባቸው አካባቢዎች በአካል በመገኘት እያንዳንዱን ቦታ በጥልቀትና በዝርዝር ክለሳ ጥናት ሲረጋገጥ ብቻ አስፈላጊው ምላሽ እንደሚሰጥ ዋና ዳይሬክተሩ አስረድተዋል፡፡

ርባቸውን ቦታዎች ብቻ በመለየት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ብቻ ዕርዳታ ለማቅረብ የተቀየሰ መሆኑ በተለይ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚኖረውን የዕርዳታ ጠባቂነትና የተረጂነት ስሜት ለመቅረፍ በእጅጉ እንደሚያግዝና የሚገኘውም አነስተኛ የዕርዳታ ሀብት ከመቼውም ጊዜ በላቀ ሁኔታ ለታለመለት ዓላማ በማዋል ረገድ ጠቀሜታውም የጎላ እንደሚሆን ታምኖበታል።

አዲስ የተቀየሰውን የዕለት ዕርዳታ አቅርቦትና አጠቃቀም አሠራር ተግባራዊ ለማድረግም የወቅታዊ ሁኔታ ክትትልና ግምገማ ሥርዓት እስከወረዳ ድረስ መጠናከር እንዳለበትና የአስቸኳይ ጊዜ ዕርዳታ ጥያቄም በክትትልና ግምገማው ግኝት መነሻነት የአካባቢዎችን ችግርና የተጎጂዎችን ትክክለኛ ፍላጎት መሠረት ያደረገ መሆን እንደሚገባው በውይይቱ ላይ ተገልጿል።

አዲሱ የዕለት ዕርዳታ አቅርቦትና አጠቃቀም አሠራር ሥርዓት በሀገሪቱ በተያዘው የልማት አቅጣጫ በተወሰኑ አካባቢዎች ሊኖር ለሚችል የምግብ እጥረትን ለመቋቋም በሚወሰደው እርምጃም በተቻለ መጠን ከልማት ጋር በማቀናጀትና በብቃት ጥቅም ላይ በማዋል ሀገሪቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ከተረጂነት ለማላቀቅ የታለመ መሆኑም ተመልክቷል።

ይኸን አዲስ አሠራር ተግባራዊ ለማድረግ በአሠራሩ ላይ እስከ ወረዳና ቀበሌ ድረስ የሚመለከታቸውን አካላት ግንዛቤ ለማስጨበጡ ሥራ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባና በዚህ ረገድ የየክልሉ አደጋ መከላከልና ምግብ ዋስትና ቢሮ ሀላፊዎች አሠራሩን ለማስተዋወቅ በግንባር ቀደምትነት መንቀሳቀስ እንደሚጠበቅባቸውና ከፌዴራል አመዝኤ አስፈላጊው እገዛ እንደሚደረግ የውይይቱ ተሳታፊዎች በጋራ ተስማምተዋል።

## ባለፉት 6 ወራት 57 ሺህ 941 ሜ/ቶን እህል ለምግብ ዋስትና አቅርቦትና ከ17 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ምግብ ነክ ላልሆነ ፍላጎት በዕርዳታ ተገኝቷል

### ከ105 ሺህ ሜ/ቶን በላይ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆነ ዕርዳታ ለተረጂዎች ተጓጉዟል።

በ1999 በጀት ዓመት ባለፉት ስድስት ወራት ውስጥ 57 ሺህ 941 ሜ/ቶን የምግብ ዕርዳታ የተገኘ ሲሆን ምግብ ነክ ላልሆነ ፍላጎት ማለትም ለውሀ አቅርቦት 7



ሚሊዮን 513 ሺህ 913 ፣ ለጤናና ለሥርዓተ ምግብ 4 ሚሊዮን 51 ሺህ 179 ፣ ለግብርናና ለእንስሳት መኖ 1 ሚሊዮን 239 ሺ 783 ፣ ለአቅም ግንባታ 184 ሺህ 450 ፣ ለማስተባበር ሥራ 2 መቶ ሺህ፣ለትራንስፖርት ድጎማ 4 ሚሊዮን 321 ሺህ 513 በአጠቃላይ 17 ሚሊዮን 510 ሺህ 838 የአሜሪካን ዶላር መገኘቱን የፖሊሲ

ባለፉት ስድስት ወራት የአስቸኳይ ዕርዳታና የልማት ሥራዎች ለሚያከናውኑ የረድኤት ድርጅቶች 190 ሺህ 357 ሜ/ቶን እህል ከመጠባበቂያ ምግብ ክምችት በብድር የተሰጠ ሲሆን ፣ ቀደም ሲል ለተለያዩ መያድና ለአመዝኤ በተለያዩ ዓመታት በብድር ከተሰጠው እህል 164 ሺህ 468 ሚ/ቶን ወደ ክምችቱ ተመልሷል።

ኘላንና ኘሮግራም መምሪያ ያዘጋጀው የ1999 በጀት ዓመት የስድስት ወር ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት መረጃ አመልክቷል፡፡

ሪፖርቱ በሚሸፍነው ጊዜ ውስጥም ከማዕከላዊ መጋዘኖች 81 ሺህ 28 ሜ/ቶን እህል ፣ 24 ሺህ 625 ሜ/ቶን አልሚ ምግብ ፣ ግምታቸው 1 ሚሊዮን 443 ሺህ 617 ብር የሆኑ ቁሳቁሶች ተረጂዎች ወደሚገኙባቸው አካባቢዎች ተጓጉዘው ተከፋፍለዋል፡፡



መረጃው ጨምሮ እንዳመለከተው ባለፉት ስድስት ወራት የአስቸኳይ ዕርዳታና የልማት ሥራዎች ለሚያከናውኑ የረድኤት ድርጅቶች 190 ሺህ 357 ሜ/ቶን እህል ከመጠባበቂያ ምግብ ክምችት በብድር የተሰጠ ሲሆን ፣ ቀደም ሲል ለተለያዩ መያድና ለአመዝኤ በተለያዩ ዓመታት በብድር ከተሰጠው እህል 164 ሺህ 468 ሚ/ቶን ወደ ክምችቱ ተመልሷል፡፡ በክምችቱ ላይ ብክነትና ብልሽት እንዳይኖርና የጥራት ደረጃውን ለመጠበቅ ለ177 ሺህ 76 ሜ/ቶን እህል የህክምና ፣ በ187 ሺህ 947 ሚ/ቶን እህል የኬሚካል ሥርጭት ሥራ ተከናውኗል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም በግማሽ ዓመቱ የአመዝ ፈንድን አቅም ለማጎልበት በተካሄደው ሥራ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ተሸከርካሪዎች ሽያጭ 668 ሺህ 918 ብር ፣ ከግምጃ ቤት ጨረታ ሽያጭ 4 ሺህ 730 በድምሩ 673 ሺህ 645 ብር ሊሰበሰብ መቻሉም ከፖሊሲ ኘላንና መመሪያ ከጠየቀው የኤጀንሲው የ6 ወር የሥራ አፈጻጸም ሰነድ አመልክቷል፡፡

## በጎርፍ አደጋ ለተጎዱ ወገኖች መርጃ ከብር 69ሚሊዮን በላይ ተለግሷል

ባለፈው ዓመት ክረምት ወራት በአገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች የጣለው ከባድ ዝናብ ባስከተለው የድንገተኛ ጎርፍ እና የውሀ መጥለቅለቅ አደጋዎች ሳቢያ ከቤት ንብረታቸው ለተፈናቀሉ እና ጥሪታቸውን ላጡ ወገኖች መልሶ ማቋቋሚያ ከሀገር ውስጥ በተለያዩ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሠራተኞች ፣ በማህበራት ፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ የግል ድርጅቶች እና ግለሰቦች እንዲሁም ከሀገር ውጭ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች አማካይነት እስከ የካቲት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ብር 69 ሚሊዮን 302 ሺህ 362 ከ58 ሳንቲም በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተለግሷል፡፡

ከዚሁ ከተለገሠው ጠቅላላ ገንዘብ ውስጥ ብር 51 ሚሊዮን 972 ሺህ 874 ከ46 ሳንቲም በማዕከል ቀሪው ብር 17 ሚሊዮን 329 ሺህ 488 ከ12 ሳቲም በድሬዳዋ አስተዳደር ውንስል በጥሬ ገንዘብ በዓይነት የተለገሠ መሆኑን ከአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኤጀንሲ የዕርዳታ ማሰባሰብ ቡድን የተገኘ መረጃ ያመለክታል፡፡



በተለያዩ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና ሠራተኞች ፣ በማህበራት ፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ የግል ድርጅቶች እና ግለሰቦች እንዲሁም ከሀገር ውጭ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች አማካይነት እስከ የካቲት 30 ቀን 1999 ዓ.ም ባለው ጊዜ ውስጥ በጠቅላላው ብር 69 ሚሊዮን 302 ሺህ 362 ከ58 ሳንቲም በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተለግሷል፡፡

በማዕከል ከተለገሠው ጠቅላላ ብር 51

ሚሊዮን 972 ሺህ 874 ከ46 ሳንቲም ውስጥ ብር 44 ሚሊዮን 155 ሺህ 487 ከ01 ሣንቲም በጥሬ ገንዘብ ቀሪው ብር 7 ሚሊዮን 817 ሺህ 387 ከ45 ሳንቲ ደግሞ በዓይነት የተለገሠ ነው፡፡

በተመሳሳይም በድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል ከተለገሠው ጠቅላላ ብር 17 ሚሊዮን 329 ሺህ 488 ከ12 ሣንቲም ውስጥ ብር 9 ሚሊዮን 201 ሺህ 549 ከ68 ሳንቲም በጥሬ ገንዘብ ቀሪው ብር 8 ሚሊዮን 127 ሺህ 938 ከ44 ሣንቲም ደግሞ በዓይነት የተለገሠ መሆኑን ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡